ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

Efdpu@aol.com www.Finote.org

በፍኖተ ዴሞክራሲ  የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ
በ መጋቢት 3 ቀን  2011 ዓም  የተላለፈ  ሐተታ

## ይድረስ ለኢትዮጵያ ሀገር ወዳድ ህገር አድን ወጣቶች በያላችሁበት ሁሉ

ታሪካችን የሚነግረን አንድ ሀቅ ኢትዮጵያን ለማዳን ወጣቶች ያላቸውን ከባድ ሚና የሚጠቁም ነው ። አዛውንት ያላቸውንና የነበራችውን ከፍተኛ ሚና የሚሽር ሳይሆን የሚያግዝና የሚያጠናክር ነው ። በየትኛውም ጊዜ ሕዝብ ሲባል ወጣቱ ብዙሃን ስለሆነ በህብረተሰቡም ሚናው ከፍተኛ ነው ። በአሁኑ ጊዜ ከ55 በመቶ በላይ ሕዝብ ከ25 ዓመት በታች ያለው ነው። ለለውጥ ሆነ ለሀገር አድን ትግሉ ወሳኝ ሚናና ቦታ ያለው ነው ። ወጣት ስንልም ወንዱን ሴቱንም ወጣት ማለታችን መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። በጣሊያን ወረራ ጊዜ ፋሺስቶቹ ወጣትና ምሁርን ለመጨረስ እርምጃ መውሰዳቸው ይታወሳል ።የጥቁር አንበሳ ድርጅት መስራችና አንቀሳቃሾች ወጣቶች ነበሩ ። ለውጥ ፈላጊዎች ። የኢትዮጵያ ተራማጆች ወጣቶች ሲሆኑ በየካቲት አብዮትም ግንባር ቀደም ሚና ነበራቸው ። ኢሕአፓንም መስርተው የታገሉትና ሕዝብን አደራጅተው ያታገሉት ወጣቶች ነበሩ--በፊውዳል ጨለማ የይቻላልን ቀንዲል የለኮሱና ታሪክ የሰሩ። ብዙ ማለት ቢቻልም በሀገር አድኑ ትግል የወጣቱ ሚና ቁልፍና ከፍተኛ ነው፤ መሆን ያለበትም ነው፤  የሚለው ነው መልዕክቱ ።

ለሀገር ወዳዱ፤ለኢትዮጵያዊው ወጣት መልዕክታችን ሀገራችንን ከጥፋት ለማዳን ተነሱ፤ ተባበሩና ትግልን አጧጡፉ የሚል ነው ። ዛሬ ሀገራችን በአደጋ ላይ መሆኗን  ማንም ሊክድ አይችልም። ደም ገብረን ታግለን ወያኔን ልናስወግድ በህብረት ስንነሳ ትግላችንን የሚያደናቅፍ ደንቃራ በአሜሪካና በአረቦች ተሰይሞብን ችግር መፍጠሩ ምስጢር አይደለም ። ተቃኝቶና ሰልጥኖ የመጣ በመሆኑም በስልት የብዙዎችን ቀልብ ሰልቦና ጭፍን ድጋፍን አግኝቶ ለተወሰነ ጊዜ አደናግሮ ሊጨፍርብንም ዕድል አግኝቶ ነበር ። ስንዘናጋ ግን ሀገራችንና ማንነታችንም  ሊነጥቀን ቸኩሎ በግርግር ለጽንፈኞች አመችቶ ኢትዮጵያን ለግንጠላና ለእርስ በርስ ጦርነት አጋልጧት ይገኛል ። ሀገራችን በአሳሳቢ አደጋ ላይ ናት ። ለገንጣዮችና ጠባብ ብሄርተኞች ሰለባ ልናደርጋት በፍጹም የሚታሰብ አይደለም ። ወጣቱ ሀገራዊ ግዴታውን መወጣት አለበት፤ግዳጅ አለበት። ሀገር አድን ግዳጅ ። ዛሬ ጎጥና ጎሳ የሚቆጠርበት ጊዜ ሳይሆን ኢትዮጵያዊነት የሚከበርበትና የሚጠናከርበት ነው ። ወጣቱ በዚህ በዚያ ተደናግሮ ዘር ቆጠራ ሳይገባ በኢትዮጵያዊነት ተባብሮ ዘረኛ ጨቋኞችን የሚፋለምበት ወቅት ነው ። ወያኔን ለቀውስ የዳረገው እኮ የሕዝብ የተባበረ ትግል መሆኑን መዘንጋት የለብንም ። የሕዝብን ሚና ሹሞቹ ሊቀሙ የሚወራጩት ከንቱ ነው ። ሹሞቹ ለተወሰነ ወራት ተጨንቀውና ተጠበው ያመጡት ምንም ውጤትና ለውጥ የለም ። ሕዝብ ነው በደሙ የወያኔን ቀውስ እውን ያደረገው ። ብዙ  ሺ ወጣቶች ናቸው ጸረ ወያኔ ሆነው ታግለውና መስዋዕትነት ከፍለው ለወያኔ ውድቀት ምክንያት የሆኑት ። አሁንም በመጀመሪያ ደረጃ ኢትዮጵያን ሊታደጋት የሚችለው ወጣቱ ነው ።

ታሪካችንን መለስ ብለን ስንመረምር በቀውጢ ጊዜ ሁሉ የኢትዮጵያ ወጣቶች በጎጥና በብሄረሰብ ሳይለያዩ አንድነታቸውን አጠንክረው ሀገራቸውን ከጥፋት አድነዋል ። ኢትዮጵያ ዛሬ የነሱ መስዋዕትነት ውጤት ናት። ሁሉም ወርቅ ዜጎች ነበሩ--ኢትዮጵያውያን ። ተፈጥሮ ነውና እንደነ ኃይለሥላሴ ጉግሳ ዓይነት ባንዳዎችም በኢትዮጵያ ላይ ሲነሱ ታይተዋል ።አርበኛ በበዛበት ባንዳዎች ብቅ ማለታቸውም ያለ ነው፤ትላንትም አይተነዋል፤ ዛሬም በገሃድ እያየነው ነው ። በየካቲት 66

ለመሰረታዊ ለውጥ የታገለው ወጣት ታሪክን ሰርቶ አልፏል። የተሰለፈውና የተሰዋው አንዳድንድ የታሪክ ላፒሶች ሲቀጥፉ እንደሚሰማው ሳይሆን ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ ነበር ። ኢሕ አፓ ራሱ ህብረ ብሄራዊ ሆኖ ከነስሙ ኢትዮጵያዊ ድርጅት ነበር፤ነውም። ይህንን ሀገራዊ ትግል ለመሸርሸር በየብሄሩ ተከፋፍሎ እንዲደራጅና እንዲንቀሳቀሥ ተደረገ። ባዕዳን የኢትዮፕያ ጠላቶችም የሀገራችንን መከፋፈል ትላንትም ዛሬም እንደሚፈልጉ እናውቃለን ። በላያችን ያመጧቸው ሹሞች ዘረኝነትን በዘረኝነት ተከተው ሀገራችንን ሊያጠፉ ሲፍጨረጨሩ እነሆ ዛሬ እያየን ነው ። ለተወሰነ ጊዜ ሹሞቹ ወጣቱንም ሕዝቡንም ሊያደናግሩ ችለው ነበር ። ተል ዕኮአቸው ከይሲና ጸረ ኢትዮጵያ ነው ብለነውም ተወግዘንበት እንደነበር አልረሳንም ። ዛሬ ግን የሹሞቹ ግብና ስምሪት ምን እንደሆነ ለማወቅ ችለናል ። ኢትዮጵያ የሚሉትን ወጣቶች እያሰረና እያጋዘ ሀገራችንን በገሃድ ሊያፈርሱ የሚለፍፉና የሚሰሩትን ግን መረን ለቋቸው ይገኛል። ባለጌ ጽንፈኞችን አቅፎ ደግፎም አለ። በኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ላይ ሰፊና ክፉ ዘመቻ ከፍተዋል ። የሕዝብን ማንነት እየሰረዙ የዘር የበላይነታቸው ለማስፈን በሚሊዮን ሕዝብን አፈናቅለው፤ የርስ በርስ ጥላቻና ግጭትን አባብብሰው ይገኛሉ። በባዶ ቃላት ድለላ ብዙሃኑን አስተኝተው ሀገር ሊቀሙን በመራወጥ ላይ ናቸው ። በአንጻሩ ደግሞ ለሕዝብ እንታገላለን ሲሉ ብዙዎቹ ቡድኖችና ድርጅቶች ለሆዳቸው እጅ ሰጥተው የዚህ የጸረ ኢትዮጵያ ዘመቻ በተጨባጭ ተባባሪ ሆነው ይገኛሉ። ሆኖም በወጣቱ ቆራጥነት አሁንም ትግሉ ቀጥሎ ኢትዮጵያውና ሕዝቧን ለመታደግ መስዋዕትነት እየተከፈለ ነው ። ትግል መስዋዕትነትን ይጠይቃል ። ሀገራንን ጠብቀው ያስረከቡን የቀድሞቹ ከጠላት ተፋልመው፤ጦርና ጋሻ ይዘው ታንኮችን ተጋፍጠው በሚሊዮን ደረጃም ተሰውተው ነው። ፋሺስቶችን ለመዋጋት ብዙ ወጣት ውድ ሕይወቱን ለሀገሩ ገብሯል። በጀግንነት፤ በጽናትና ኩራት ። የኢትዮጵያ ወጣቶች ታሪክ የሀገር ወዳድ ጀግና ታሪክ እንጂ የዘረኞችና ባንዳዎች ቅራሪ አይደለም ። ይህን መገንዘብ ያሻል ።

ወጣቶች ትኩስና አዲስ ሀይል በመሆናቸው ወደ ዕድገትና ወደ ነገ ዕይታቸው የሰላ ነው ። ወደፊት እንጂ ወደኋላን አይወክሉም ።የሀገር አንድነትንና የሕዝብ ብልጽግና ይወክላሉ እንጂ ወደ ኋላ ተመልሰው ጎጥ ቀልሰው እርመኔ ሆነው ደም እርስ በርስ አይፋሰሱም ። የኢትዮጵያን አንድነት ጠብቆ ሌሎች ሀገሮች ጋርም ተባብሮ የባዕዳንን ወረርና ብዝበዛ ለመቁቋም ያልማል እንጂ ሀገርን በጎጥ ሸንሽኖ ማፍረስን ግቡ አያደርግም ። የጥላቻና የክፍፍል ሀይሎች በዕድሜ ወጣት ከሆኑም በይዘት ግን የበሰበሱና የገረጀፉ ናቸው ። ወጣቱ ዘረኛ ሊሆን አይጠበቅም--ለዚህም ነው ሁሉም ኢትዮጵያዊ ወጣት ዘረኞቹን አስወግዶና ህብረቱን አጠንክሮ ሀገር አድን ትግል ያካሂድ በሚል ጥሪ የምናስተላልፈው ።ዛሬ የመደናገሪያ ጊዜ አልፏል፤ አክትሟል። አውቀንባቸዋል። ኢትዮጵያን ሊያጠፉ እንጂ ሊታደጉ እንዳልተላኩ ገብቶናል ። ወያኔነትን በሌላ መልክ ሊያስቀጥሉ የመጡ ኦሮሚኛ ተናጋሪ ወያኔዎች መሆናቸውንም ነቅተንባቸዋል ። ከሻዕቢያም መለጠፋቸው ከሰላም ፍለጋ ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌለውም የተነገረው ሀቅ ነው ። የፖለቲካና ኤኮኖሚ ሂደታችንም ሹሞቹ ሕዝብ ሳያማክሩ በራሳቸው የወሰኑ በመሆኑ ሀገራችን ለባዕድ በዝባዦች ተጋልጣ ልትሰጥ ዝግጅት መደረጉ ለእኛ ምስጢር አይደለም ። በዘረኛ ወሮበላ መንጋ ላይ እምነቱን የጣለው የሹሞቹ አገዛዝ ይዘቱና አካሄዱ አለምንም ጥርጥር ጸረ ኢትዮጵያ ነውና ወጣቱ ቆርጦ በመነሳት ሊታገለው ይገባል ።

ተማሪ አስተማሪ ወጣቶች፤ በአገዛዙ ሰራዊት ውስጥ ያላሁ ወጣቶች፤ በገጠር ነዋሪ ወጣቶች፤ ወጣት ላባደሮች፤ ሁላችሁም የኢትዮጵያ ብርቅዬ ልጆች ሀገራችንን ከጥፋት ለማዳን ተባብራችሁ ተነሱ ። ትግል በድርጅት ነውና ተደራጁ፤ ሀቀኛ ሀገር ወዳድ ድርጅቶችን እርዱ፤ ተባበሩና ተሰለፉ። ጊዜ ለአፍራሾች አትስጡ ። እያየናቸው ሀገራችን ኢትዮጵያን እንዳያፈርሱ

ከወዲሁ እንነሳባቸው። ንቀውናልና አምጸን ትምህርት እንስጣቸው ። ሀይል ሁሌም የሕዝብ ነውና በትግል ከንቱነታቸውን እናረጋግጥላቸው ።ትግላችንን ከማደናቀፋቸው በፊት አሳይተን የነበረውን ህብረትና ቆራጥነት ዳግም እናሳያቸው ። የወረቀት ነብርነታቸውን እንዲገነዘቡ እናድርጋቸው ።

የኢትዮጵያ ወጣቶች የጀግንነት ታሪካችሁን አድሳችሁ በዘረኞቹ ላይ በህብረት ተነሱ። አብረናችሁ ነን እንላለን።

ሕዝባዊ አመጽ ይፋፋም !!

ዘረኝነትና ባንዳነት ይወገድ !!

ኢትዮጵያዊነት ያቸንፋል !!